# Grenfell Tower community update: October 2026 – Amharic/ አማርኛ

**የግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) የማህበረሰብ ወቅታዊ መረጃ፡- ኦክቶበር 2026**

ግሬንፌል ታወርበአደጋው በጣም ለተጎዱት ሰዎች ጥልቅ ግላዊ ትርጉም እንዳለው እና መሬቱ ለቤተሰቦቹ የተቀደሰ እንደሆነ እንገነዘባለን።

ታወሩን በጥንቃቄ የማፍረስ ስራችን አስመልክቶ ወቅታዊ መረጃ እንዲኖርዎት እንፈልጋለን። በዚህ አዲስ መረጃ ውስጥ ስለሚከተሉት ተጨማሪ ማወቅ ይችላሉ፡-

- **ስለ አቧራ እና ንዝረት መረጃን መከታተል**
- **ስለጤና እና ደህንነት**
- **እንዴት ከእኛ ጋር መነጋገር ወይም ተጨማሪ መረጃ ማግኘት እንደሚቻል**

ያለፈው መረጃዎችን በዚህ ማየት ይችላሉ: www.gov.uk/grenfell-community-updates

## የድምፅ ብክለት፣ አቧራ እና ንዝረት የተመለከተ መረጃን መከታተል

መንግስት በግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) ጣቢያ ላይ የሚሰራው ሁሉም ስራ በከፍተኛ ጥራት መከናከወኑን ለማረጋገጥ ቁርጠኛ ነው። የማህበረሰቡ እና በጣቢያው ላይ የሚሰሩ ሰዎች ጤና እና ጥበቃ ቅድሚያ የምንሰጠው ጉዳይ ነው። በስፍራው ላይ ስለ አቧራ፣ ንዝረት እና የድምፅ ብክለት የቀጥታ መረጃዎችን የሚሰበስቡ መከታተያዎች ይገኛሉ። መረጃው በየወሩ ይታተማል። የቅርብ ጊዜ ሪፖርቶችን ለማየት፣ እባክዎን ከታች ያሉትን ሊንኮች ይጫኑ፡-

የአቧራ ክትትል ሪፖርት ከጁላይ 27 እስከ ኦገስት 30፣ 2026
የንዝረት ክትትል ሪፖርት ከጁላይ 27 እስከ ኦገስት 30፣ 2026
የድምፅ ክትትል ሪፖርት ከጁላይ 27 እስከ ኦገስት 30፣ 2026

ሥራው በሚከናወንበት ወቅት የዩኬ የጤና ደኅንነት ኤጀንሲ (UK Health Security Agency፣ UKHSA) በግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) ዙሪያ ያለውን የአየር ጥራት መገምገሙን እና መከታተሉን ይቀጥላል። ሪፖርቶቹን በየወሩ ያትማል። የቅርብ ጊዜ ሪፖርቱን እዚህ ማግኘት ትችላላችሁ፡-

የአካባቢ ክትትል ከግሬንፌል ታወር እሳት  አደጋ በኋላ - GOV.UK

## የጤና እና የደኅንነት ድጋፍ

ከአንድ ሰው ጋር መነጋገር ከፈለጉ፣ የ Grenfell Health and Wellbeing Service ለህፃናት እና ለአዋቂዎች የሚሰጥ ነፃ እና ምስጢራዊ የ NHS አገልግሎት ነው:: ድጋፍ ግረንፈል ታወርን (Grenfell Tower) በጥንቃቄ ለማፍረስ ስሜታዊ እና አካላዊ ደህንነት ድጋፍ ለሟች ቤተሰቦች፣ በሕይወት ለተረፉ እና በቅርብ ማህበረሰብ ውስጥ ላሉ ነዋሪዎች መደረጉን ቀጥሏል። ከአንድ ሰው ጋር መነጋገር ከፈለግአችሁ፣ የሚከተሉትን ማድረግ ትችላላችሁ፡-

- ወደ Grenfell Wellbeing አገልግሎት በ 020 8637 6279 (ከ8am እስከ 8pm፣ በየቀኑ) ይደውሉ።
- በድንገተኛ ጊዜ የማዕከላዊ እና የሰሜን ምዕራብ ለንደን የNHS ፋውንዴሽን ትረስት (Call Central and North West London, CNWL) ነጠላ የመድረሻ አማካሪ መስመርን በሚከተለው ቁጥር ይደውሉ፡-
  0800 0234 650 (በቀን ለ24 ሰዓታት፣ በሳምንት ለሰባት ቀናት ክፍት ነው)
- ኢሜል፡- grenfell.wellbeingservice@nhs.net
- ለተጨማሪ መረጃ: www.grenfellwellbeing.cnwl.nhs.uk ን ጎብኙ

ስለሚገኙ አገልግሎቶች የቅርብ ጊዜ መረጃ ለማግኘት፣ www.grenfell.nhs.ukን ይጎብኙ

## ከእኛ ጋር እንዴት መነጋገር እንደሚችሉ ወይም የበለጠ ለማወቅ

መረጃን ለእርስዎ ጠቃሚ በሆነ መንገድ ማጋራት እንፈልጋለን። መደበኛ የሆኑ አዳዲስ መረጃዎችን እና ማብራሪያዎችን ማካፈላችንን በዚሁ እንቀጥላለን፡- www.gov.uk/grenfell-community-updates

እባክዎ በዚህ ኢሜል ያድርጉልን: GrenfellTowerSite@communities.gov.uk ለ:

- ከእኛ ጋር ወይም ከግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) ጣቢያ ዋና ተቋራጭ ከሆኑት ከዲሲዩኬ (DCUK) ጋር እንዲነጋገሩ ያመቻቹ።
- ታወሩን በጥንቃቄ ለማፍረስ ስለሚከናወነው ሥራ ያለዎትን ማንኛውንም ጥያቄ ይጠይቁን ወይም ማንኛውንም ስጋት ያጋሩ።
- መደበኛ ዝማኔዎቻችንን በቀጥታ ወደ እርስዎ ኢሜይል እንድልክ ሊጠይቁን ይችላሉ።
- ከእኛ ጋር በሚያደርጉት የመረጃ ልውውጥ እና ተሳትፎ ላይ ያለዎትን አስተያየት ማካፈል ከፈለጉ፣ እባክዎን ያጋሩን:: አስተያየትዎ እንቀበላለን።

በግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) ላይ የቅርብ ጊዜ መረጃዎችን ለማግኘትና ለኢሜል ማሳወቂያዎች ለመመዝገብ፣ እባክዎን ወደሚከተለው ድረገጽ ይሂዱ፡- www.gov.uk/grenfell-community-updates ወይም ከታች ያለውን የQR ኮድ ስካን አድርጉ።

**የግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) ጣቢያ አስተዳደር ቡድን የቤቶች፣ ማህበረሰቦች እና የአካባቢው አስተዳደር ሚኒስቴር**